1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12269 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 32718 ሰኔ 29 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡
2. የምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 14676 የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት አጽንተናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 45161

ታህሣሥ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** 1. እናኑ ጀንበሬ - ቀረቡ፡፡

2. ላቀች ጀንበሬ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት - ወኪል በአንተአምላክ አንተነህ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ የከሳሾች እናትና አባት በሕይወት በነበሩ ጊዜ በደሴ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል በገዙት ቦታ ላይ ቁጥር 045 እና 046 የሆኑ ቤቶችን ሠርተዋል፡፡ ከእነዚህ ቤቶች ውስጥ ቁጥር 045 የሆነው ቤት በአዋጅ 47/67 በትርፍነት ያልተወረሰ ሲሆን ከሳሾች በማናውቀው ሁኔታ አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛ ተከሣሽ አከራይቶት ይገኛል፡፡ ከሣሾች ቤቱ እንዲመለስልን ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አመልክተን ጉዳዩ አይመለከተኝም በማለት ይህንኑ በደብዳቤ አረጋግጦናል፡፡

ስለሆነም አንደኛ ተከሣሽ ቤቱን ይዞ ለሁለተኛ ተከሣሽ በማከራየት ላይ የሚገኘው በአዋጅ ባልተወረሰበት ሁኔታ ስለሆነ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡን ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንልን ብለናዋል፡፡

የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ክስ የቀረበበት ቤት በአዋጅ ተወርሷል ወይንስ አልተወረሰም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ቀደም ሲል ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ይህንኑ ቤት አስመልክቶ አቤቱታውን ሳይቀበለው መቅረቱ ቤቱ አልተወረሰም ተብሎ ውሣኔ እንደተሰጠ የወረዳው ፍ/ቤት በመቁጠር ለከሣሾች ሊመለስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም ብሎ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ ሽሯል፡፡

የሥር ከሣሾችም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱተው ለሰበር አይቀርብም ብሎ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ የደሴ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አመልካቾች ከፕራይቤታይዜሽን ኤጀንሲ ውሣኔ አላሰጡም በሚል ምክንያት የወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ መሻሩ አግባብነቱን ለማጣራት አቤቱተው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙንም በቃል አከራክሯል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾች ክስ ያቀረቡት በውርስ የተላለፈልንን ቤት ተጠሪዎች ከሕግ ውጭ ይዘው ስለሚኙ ያስረክቡን በማለት ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና በዚህ ችሎትም በተደረገው ማጣራት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ይዘው የሚገኙት ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የኪራይ ውል መነሻነት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ክርክር የተነሳበት ቤት ለረጅም ዓመታት በመንግሥት እጅ የቆየ ከሆነ አመልካቾች ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ተፈቅዶላቸው ባለንብረት ስለመሆናቸው ወይንም ደግሞ ከአዋጅ ውጭ ያለአግባብ ተወስዶብናል የሚሉ ከሆነም ለሚመለከተው አካል አቤቱታ አቅርበው ውሣኔ አግኝተው ባለመብት ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ አመልካቾች በዚህ መልኩ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ካላረጋገጡ ደግሞ ከመነሻውም ቢሆን ክስ ባቀረቡት ነገር መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ መንግሥት ተረክቦ ሲያስተዳድራቸው የነበሩ ቤቶች ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ክስ የሚያቀርብ ወገንም ከላይ እንደተጠቀሰው በአዋጅ 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል አቤቱታ አቅርቦ ውሣኔ አንኝቶ ባለመብት መሆኑ ካልተረጋገጠ ክስ በቀረበበት ነገር ላይ መብት ወይም ጥቅም እንደሌለው እንደሚቆጠር ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14094 የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም በተያዘውም ጉዳይ አመልካቾች ቤቱ ሊመለስልን ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ባላረጋገጡበት ሁኔታ ስለሆነ የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ቤቱ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት የሰጠውን ውሣኔ የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተለየ ምክንያት ቢሽረውም ከውጤት አኳያ ግን የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>